# ማን ያውራ የነበረ 2

የፖለቲካው መስክ አያደር የጨረባ ተዝካር ዓይነት ትርጉም አልባ ጫጫታ የበዛበት የውዥንብር መናህሪያ መስሎ መገኘቱን መካድ አይቻልም። በቅርቡ ኣንድ የፖለቲካ ድርጅት መሪ የራሱን አሳፋሪ ባንልበት አጠያያቂ የሆነውን ደርጋዊ ታሪኩን ዘንግቶ ደርግን የታገለን ድርጅት ወንበዴ ብሎ ከመ- መንግስቱ ሲዘልፍ ተደምጦ ነበር። የፖለቲካ ትግል ለስልጣን ነው መባሉ ትክክል ቢሆንም ከዚህ ባሻገር ደግሞ ትግል የራዕይ የፕሮግራም ውጤት ነው።ዛሬ ራዕይ የምንለው ደግሞ ትላንት ርዕዮተኣለም ይባል የነበረው ነው።

ኢህአፓና የርዕዮተ አለም ጥያቄ የሚለውን ስናጤን ደግሞ ድርጅቱ ከተመሰረተበት ጊዜ ትግሉን በተጠና ራዕይ አጅቦና መርቶ ለማስኬድ መሞከሩን እናያለን። በንጉሰ ሃይለስላሴ ዘመን ስርዓቱ የጥገና ለውጥን እንኳን መቀበል ያቃተው ስለነበርና በአለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ የነጻነት ትግሎች በሶሻሊስት ሀገሮች ተደግፈው ይካሄዱ ስለነበርም ሆነ የተራማጁ ርዕዮትም ክልክል ስለነበር ለውጥ ፈላጊው ክፍል ወደ ግራ ማዘንበሉ የግድ ነበር ማለት ይቻላል።በወቅቱ አሜሪካ የንጉሱ ደጋፊ ስለነበርም (ዛሬ ወያኔን ደጋፊው ፖል ሄንዚ ያኔ በኣመሪካን ኤምባሲ ሰላይ ሆኖ እየሰራ የስርአቱ ዋርዲያ ነበር) ያሜሪካ ጠላት የነበረው የሶሻሊስት ሰፈር የለውጥ ፈላጊዎች አጋርም ነበር። ስር ነቀል ለውጥ ፈላጊው ተራማጁ ክፍልም ማለትም ኢሕአፓን ጨምሮ ራዕያቸው ሶሻሊስታዊ መሆኑም ከዚሁ ተያይዞ በዚሁ የሚገለጽ ነው። ሰው እንድዘመኑ መባሉ ያለ ከመሆኑ ሌላ አንድን እንቅስቃሴ ስንመረምር የነበረብትን ጊዜና ሁነታ ማጤንም ግዴታችን ነው። ኢሕአፓ የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም አስቀዳሚ ነበርናም ስልጣን የሰፊው ሕዝብ መሆን አልበት ከሚለውና የሰርቶ አደሩን ሙሉ መብት ከሚያውቀው ርዕዮት ሊርቅ አይቻለውም ነበር ማለትም ትክክል ይሆናል። ይህ ቢባልም ቅሉ አኢሕአፓ በኣስተሳሳብ ይመስሉኛል በሚል ከባዕድ ሀገሮች ኢትዮጵያን የሚጎዳ ትዕዛዝ ተቀብሎ ሆኖ ሀገርን እንደወያኔ ለባዕድ አሳልፎ ሰጥቶ አያውቅም።

ታዋቂው ገጣሚ እንዳሉት “ ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም/ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም” ነውና በመሰረቱ አድሃሪ ከመሆን፤ኋላ ቀር ከመሆን፤ጸረ ለውጥ ከመሆን፤ጸረ መብት ከመሆን፤የብዙሃኑን መብት ተቃዋሚ ከመሆን ተራማጅና ግራ ክንፍ መሆኑና ለብዙሃኑ መብት መቆሙ የሚመረጥ ነው። ኢሕአፓ ከሕዝብ ተዋህዶ የታገለ ድርጅት ነውናም ሕዝብ ምን ይፈልጋል ሲልና ይህንኑም ሲረዳና በተጨባጭ ተመክሮም ከራዕዩ ውስጥ የተሳሳተውን ሲገነዘብ የማንንም ትዕዛዝ ሳይጠብቅ አስፈላጊውን

እርምት አድርጎ አቋሙን አስተካክሏል። ገደብ የለሽ ዴሞክራሲ ይል የነበረውን ከመድብለ ፓርቲ ስርኣት አስፈላጊነት ጋር አያይዞ፤የብሄረሰቦች መብት ይል የነበረውን ከግንጠላ በመለስ በዴሞክራሲ ክልል መመለስ አለበት ብሎ፤ለኤርትራ ችግር የፌዴሬሽን ምላሽን ሰጥቶ፤የአርሶ አደሩን የመሬት ባለቤትነት መብት ተቀብሎ፤የቅይጥ ኤኮኖሚን መርህ አስቀድሞ ወዘተ ተገቢውን ፕሮግራም ያጸደቀው ወያኔ የነቃ መስሎት የኣልባኒያ ኮሙኒዝም ተከታይ ነኝ ብሎ ወደ ባሰ ጽንፍ ሲወነጨፍ ነበር። የዛሬ 21 ዓመት በፊት ማለት ነው። ራዕይ የሌለው ድርጅት መሪ የሌለውና በትሩ የጠፋበት አይነስውር ጋር ይመሳሰላል። አንዳንዶች የድርጅታችው ራዕይ መሪ ተብየዎቹን ለስልጣን ቅርጫ ከማድረስ ሌላ አያካትትም። እሳችው የተከበሩቱ መሪ ተብየው ለቤተመንግስት ከበቁልን ሌላ ምን ፈልገን ባዮች ናችውማለት ነው።

ዛሬ ኢሕአፓ ክቡር አድርጎ ለያዛችው መሰረታዊ መርሆዎቹ መንስዔውና ቀጣዩ ማጠየቂያው የብዙሃኑ ጥቅም ነው። ለጥቂቶች ጥቅም የቆሙ ድርጅቶች አሉ።ከኢሕአፓ ይለያሉ። መብት ለምርጦች፤ለጥቂቶች የሚሉና ብዙሃኑን የሚንቁ አሉ። ከኢሕአፓ በጣም ይቃረናሉ። አርሶ አደሩና ላባአደሩ ሳይሆን ሞልቃቃውና ህሊና ቢሱ ነገደ-ከርስ ነገደ-ሼራተኑ የሚቀድምባችው አሉ። ኢሕአፓ ከእነዚህም ይለያል። ዴሞክራሲ ብለው ቢለፍፉም ይህ ለእነሱ የምርጦችን፤የጥቂቶችን፤የከበርቴውን፤ የተማረውን ወዘተ ብቻ ጥቅም ማስጠበቅ ይመስላቸዋል። ኢሕአፓ ከእነዚህም

መሰረታዊ ልዩነት አለው። የኢሕአፓ ርዕዮት የብዙሃኑ ነው። ዴሞክራሲ ሲልም ለብዙሃኑ መብትን የሚያጎናጽፍ ማለቱ ነው። ይህም መብት ገደብ የለሽና ያልተሸራራፈ መሆን አለበት ይላል። መሬት ላራሹ፤መብት ለላባደሩ ሲልም ይህንኑ ለማስረገጥ ነው። በኤኮኖሚው መስክም ለሀገር በቅሉ ነጋዴና ባለሃብት ቅድሚያን እየሰጠ በሌላ በኩል ደግሞ ሰፊው ሕዝብ ሳይበዘበዝና ለአስከፊ ድህነት ሳይዳረግ ሊኖር የሚችለበትን ሁኔታ እውን ማድረግ ይፈልጋል። የሰፊው ሕዝብ መብት መረጋገጥ፤ የብሄረሰቦች መብት መከበር፤ የሴቶችና የህጻናት መብት መረጋገጥ፤የሕዝብ የጡረታ መብት እውን መሆኑና በአጠቃላዩም ብዙሃኑ በሃገራቸው ባለሙሉ መብት ሙሉ ዜጋ መሆናችው ተቀዳሚ ነው ሲል ኢሕአፓ ያምናል። ስለዚህም ዛሬ ኢሕአፓ ሰፊውን ህብረተሰብ በሚጠቅም ዴሞክራሲ የሚያምን ማለትም በህብረተሰባዊ / ሶሻል / ዴሞክራሲ መርህ የሚመራ ድርጅት ነው።

ስለዚህም ድርጅቱ ከሌሎች የሚለይባችው በርካታ መሰረታዊ አቅዋሞች አሉት። ዴሞክራሲን በሰበብ አስባቡ ሊገድቡ ከሚነሱት ጋር አይስማምም። የጭቁን ብሄረሰቦችን መብት ከሚቃወሙ ጋር አይገጥምም። ጭቁኑ አርሶ አደር ሊበዘበዝና ሊመዘበር የተፈጠረ ከሚመስላችው ጋር፤ ላባደሩ መበዝበዙ የተፈጥሮ ህግ ነው ከሚሉ ጋር፤ ሴቶችን መጨቆን ትክክል ነው ከሚሉ ጋር፤ የሀገርን ሳይሆን የባዕድን ጥቅም ከሚያስቀድሙ ጋር፤ የሕዝብን አንድነት ከሚቃረኑ ጋር፣ ኋላ ቀር ልምዶችን መቀጠል ከሚሹ ጋር፤
ትምክህት ወይ ጠባብነትን ከሚገፉ ጋርና በግልጽም/ ሆነ በሽፍንፍን የጭቆና ስርዓትን ክሚመኙ ጋር ኢሕአፓ መሰረታዊ ልዩነት እንዳለው ቀጥሏል ። ኢሕአፓን በዚህም በዚያም የሚከሱና የሚውነጅሉ ክፍሎች ለምን ይህን አቅዋም እንደያዙ ለመረዳት የድርጅቱን መሰረታዊ አቅዋሞች ማወቅ የግድ ይሆናል። በሌላ በኩል ግን ራሳችውን የቀኝ ክንፍ ወይም የካፒታሊስት ስርአት ደጋፊ አድርገው የሚውስዱት ክፍሎች በመሰረቱ የነቃ ቀኝ ወይም የበሰለ የቀኝ ድርጅት አቅዋም የገባቸው አይደሉም። የባዕድ ጥገኛ አቅዋም አላቸው እንጂ ብሄራዊነትን አያንጸባርቁም። የብሄራዊ ከበርቴው ደሞክራሲ ራሱ አይዋጥላችውም። ከልባቸው ጸረ

ዴሞክራሲያዊ ናችው። በሕዝብ እኩልነት አያምኑም። ትምክህተኛ ወይም ጠባብ የሚለው ይበልጥ ይገልጣችዋል። የቀድሞውን የብዝበዛና ጭቆና ስርኣት በቁጥታም በሽፍንፍንም ለመመለስ የሚመኙ ናችው።

ድርጅቶች የሚገመገሙት ስለራሳችው በሚለፍፉት ሳይሆን በተግባራቸውና በተጭባጭ ሚናችው በመሆኑ ነጋ ጠባ ራሳችውን ዴሞክራሲያዊና ለመላ ኢትዮጵያ የቆሙ ኣስመስለው የሚያቀርቡትን ወደ ጎን በመተው ተጨባጭ አቅዋማችውና ስራቸው/ግብራቸው መመርመር ይኖርበታል። ይህ ከተደረገም የድርጅቶችን ማንነት በትክክል ማውቅ ይቻላል። ማን በሃቅ ለዴሞክራሲ እንደቆመ፤ማን እየቀጠፈ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል። በኢሕአፓ ላይም ለምን አምባገነናዊ ሃይሎች እንድሚዘምቱብትም መረዳት የሚቻል ይሆናል። እታገላላሁ የሚል ድርጅት ራዕይ/ርዕዩተዓለም ያሻዋል። የሌላ ድርጅት ፕሮግራም ገልብጦ መገኘቱ በረጅሙ አያዋጣም። ሁሉም ድርጅት በግልጽ በጥቅም በመደብ በተከፋፈለው ህብረተሰብ ውስጥ ግልጽና ጎራን የለየ አቅዋም ያስፈልገዋል። ኢሕአፓ ስልፌ ክሰፊው ሕዝብ ጋር ነው ሲል ጎራውን ለይቶ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ለሀገርና ለሕዝብ እንታገላላን የሚሉ ፤ሃይሎች ተጨባጩ ሁኔታ የግድ ብሎ ሃገርን ለማዳን መተባበር ሲኖርባችው በዝርዝር አቅዋሞችና ጉዳዮች ላይ ያሏቸውን ልዩነቶች ወደ ጎን በመተው ሀገርን ለማዳን በመለስተኛ ፕሮግራም ዙሪያ መተባባር መቻል ኣለባችው። ራዕይ ወይም ርዕዮተዓለም ቀይዶ ይዞ ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር የሚያጋጨን ሳይሆን ተጨባጩን ሁኔታ በሚገባ አጢነን የሕዝብን ፍላጎት ተረድተን ተገቢውን አቅዋምና መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችለን መሆን አለበት። አንዳንድ ድርጅቶች ያወቁ፤የነቁ የበቁ መስሏችው ከብሄረስብ ድርጅቶች ጋር ኣንሰራም፤ የተራማጅ አቅዋም ካላቸው ጋር አናብርም ወዘተ ሲሉ ይደምጣሉ። ይህም ብስለት ሳይሆን የትግልን ሀ ሁ አለማወቅ መሆኑን ገና አልተረዱትም። በግልባጩ ሌሎች ደግሞ ከአድሃሪዎች፤ከትምክህተኞች፤ክደርግ ሎሌዎች፤ከባዕድ አሽከሮች፤ ከህሊና ቢስ ከበርቴዎች ጋር ከቶም አናብርም ሊሏችው እንደሚችሉ አልገባችውም።

ኢሕአፓ የራዕይን አስፈላጊነት ጫና ሰጥቶ ቢያቀርብም፤ ዛሬም ለብዙሃኑ፤ለጭቁኖች መብትና ዴሞክራሲ የቆምኩ በሶሻል ወይም ህብረተሰባዊ ዴሞክራሲ የማምን ሕዝባዊ ድርጅት ነኝ ብሎ ቢሰፍም በራዕዮት ግትርነት በመያዝ ወይም ሀገርን ለማዳን መደረግ ያለበትን ከማድረግ የሚሸሽ አይደለም። ድርጅቱን የሚጠሉት ባዕዳንም ህገራዊ አቅዋሙንና አልበገር ባይነቱን ጠልተው ነውና የሚቀይረው አይኖርም። በጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች መጠላት ጸጋ እንጂ መርገም ኣይደለምና ነው። በመሰረቱ ለሕዝብ ቆምናል የሚሉ ድርጅቶች እገሌን ማስምረጥ ወይም ለስልጣን ማብቃት ከሚል ውሱን ዓላማ በበለጠ ሕዝባዊ ራዕይ ሊኖረው ይገባል። ኢሕአፓ ሕዝባዊ ራዕይ ነበረው፤ዛሬም ኣለው። ለሕዝባዊ ደሞክራሲ የቆመ ድርጅት ነው። ራዕዩ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ክብር ማስከብርና የጥቂቶችን ሳይሆን የብዙሃኑን መብት በሁሉም መስክ ማረጋገጥ ነው። ይህን ዓላማ ከሚጋሩ ጋር ኢሕአፓ ምንም ጠብ የለውም። በፖለቲካው መስክም የሚፈለገው ተመክሮ አለውናም ለርዕዮት የምንስጠውም ቦታ ተገቢውን ነው። የልዩነቶችንም ሚዛን ያውቃል። መለስተኛን ቅራኔ አቢይነትን አይሰጥም። ጠላትና ወዳጅን ይለያል። የወዳጅ ጎራንና የህብረት ክንድን አያዳክምም። ራዕየ ውሱን-ብኩን ሆኖም በእርባና ቢስ ወይም የውያኔ ፓርላማ ለሚገኝ ወንበር ሲል አይንበረከክም። ራዕዩ ሕዝባዊና ጽኑም ነው። በመሆኑም ለሕዝብ መብት በመታገሉና ለኢትዮጵያ ክብር በመቆሙ የተነሳ ኢሕአፓ አጠፋሁ ብሎ ከማንም ይቅርታ አይጠይቅም። በሕዝብ ሙሉ መብትና በሃገር ፍጹም ሉዓላዊነት ላይ ኣልተደራደረም ፤ ወደፊትም አይደራደርም። ይህ ለመለስ መንጋም ሆነ ለሌሎች ግልጽ የሆነ ይመስለናል።